# <u>በካሊፎርኒያ የተለያዩ ከተሞችና በላስቬጋስ ከተማ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ስለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሰራር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተካሄዱ</u>

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጪ ሀዋላዎችና ኤን አር/ኤን ቲ ሂሳቦች ዳይሬክተር የሆኑት ወ/ይ ሐይማኖት አማረ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን የተሳካ ለማድረግ እየተጫወተ ያለው ሚና፣ ባንኩ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል በተለይ የዳያስፖራ አካውንት አከፋፈትና አጠቃቀም፣ በህጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ስለሚላክበት አሰራር /ሃዋላ/ በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በቅርቡ በተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ላይ ለማህበረሰቡ ገለጻ አደረጉ።



<u>ወ/ይ ሐይማኖት አማረ  በትላንትናው ዕለት በሳንዲያጎ ገለጻ ሲያደርጉ</u>

ይህ ሰፊ ገለጻ ሐምሌ 30 ቀን በላስቬጋስ ፣ ነሐሴ 3 ቀን በሎስአንጀለስ፣ ነሐሴ 4 ቀን በቤይ ኤርያ/ኦክላንድ/ እና ነሐሴ 8 ቀን በሳንዲያጎ ከተሞች ተደርጓል። በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በውጭ ምንዛሪ የሚከፍቱትን ተቀማጭ ሂሳብ አከፋፈት ስላለው ጠቀሜታና ለዳያስፖራው በተሰጠው ማበረታቻ ባንኩ ሶስት ዓይነት የባንክ

አካውንቶችን መክፈት እንደሚችልና በዚህም ራሱን ጠቅሞ አገሩን መጥቀም እንደሚችል በመግለጽ፣ ዝርዝር አሰራሩን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ እንዲወሰድ አስረድተዋል።

በመቀጠልም በህጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ ያሉ የሀዋላ ድርጅቶችና ባንኩ በአከባቢያችን የስራ ግንኙነት ያላቸው የባንኮች ዝርዝር፣ ባንኩ የቪዛና ማስተር ካርድ ለመስጠት እያደረገ ያለውን ቅድመ ዝግጅት፣ የኦን-ላይን ባንኪንግ አሰራር መዘርጋቱና፣ የአገራችንን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቡን እንዲመታ ባንኩ እያደረገ ያለውን የፋይናንስ ድጋፍ እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙርያ ለተሰብሳቢዎች ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በአገር ውስጥና በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ "እንደጀመርነው እንጨርሰዋለው" በሚል በገባው ቃል መሠረት ግድቡ በታቀደለት መሰረት በሚገባ እየተከናወነ በመሆኑና ባንዲራ ፕሮጀክት በመሆኑ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ከተሰብሳቢዎችም ለተነሱ ከባንኩ አሰራር ጋር በተያያዘ ለቀረቡት ጥያቄዎች እና አስተያየቶችን አጥጋቢ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ ተሰብሳቢዎችም ከገለጻው ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘታቸውንና በገለጻው ላልተሳተፉ የማህበረሰቡ አባላት ገለጻውን እንደሚያስረዱና የባንክ አካውንት እንዲከፍቱ ቃል ገብተዋል። በየቦታው በተደረጉ ስብሰባዎች የነበሩት ተሳታፊዎች ዳይሬክተርዋ በሚመሩት ስራ ላይ ያለው ቀላልና ቀልጣፋ የስራ ግንኙነት በሚመለከት ያላቸውን አድናቆትና ምስጋና ገልጸዋል።